# አገር ቀና ትበል

ቅጥረኛው ወያኔ ፣ አገር አስገንጥሎ
በዘር በሃይማኖት ፣ ህዝቦቿን ከፋፍሎ
ንብረቷን አራቁቶ ፣ እንዳለ ጠቅልሎ
ኢትዮጵያ እንዳትኖር ፣ ለዘላለም ገሎ
አኮብኩቧል ዛሬ ፣ ሊወጣ ኮብልሎ ።

አገሬ የምትል ፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ
እርስ በርስ መናቆር ፣ ቀርቶ መቋሰሉ
ባዕዳን ባገርህ ፣ ቅርጫ ሲጣጣሉ
ቁጭ ብሎ መታዘብ ፣ ይብቃህ ማስተዋሉ
ስጋህን መትረውት ፣ ቋምጠዋል ሊበሉ ።

ኢትዮጵያ አገራችን ፣ የበላይ ያሉላ
የምዬ ምኒሊክ ፣ የካሳው መቅደላ
ወያኔ የሚባል ፣ አራሙቻ አብቅላ
አገርና ህዝቡን ፣ ሲማግድ ለተኩላ
ጀግናው ያገሬ ልጅ ፣ ምነው ይላል ችላ ?
እንዴት በቀን ጅቦች ፣ እማማ ትበላ ።

ህፃን ሽማግሌ ፣ ሴት ወንዱ ጎረምሳ
ታሪክ ተረካቢው ፣ የኢትዮጵያ አንበሳ
በናት ጡት ነካሾች ፣ አገርህ ኮስሳ
ስትሆን እያየህ ፣ ማምረቻ የሬሳ
ለምን አይቆጭህም ፣ ምነው አትነሳ ?
        መቿገር አይወገድ ፣ ባማላጅ ወቀሳ
        ይልቅ መሳሪያህን ፣ ጦር ጋሻህን አንሳ !
አገር ምድር ይሙላ ፣ በጠላት እሬሳ
አጥንት ተከስክሶ ፣ በደም እረስርሳ
የወያኔ ድባብ ፣ ካገር ላይ ይነሳ
መመኪያ ሀገርክን ፣ ከምታያት ፈርሳ
አገር ቀና ትበል ፣ ታገግም ትነሳ ።

ታዛቢው … February 24, 2012